በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

??/? /?? ? 221154
?? 23/9/2014 ?/?

ዳኞች ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች - ወ/ሮ ዮዲት ብርሃኑ፡- ቀረቡ

ተጠሪ - አቶ ሳምሶን አምባዬ፡- ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች የካቲት 9 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 275237 ጥር 5 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 256800 ሚያዝያ 18 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታዋን በማቅረቧ ነው፡፡ ቅሬታዋም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የምትቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የምትለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ ቀለብ ሰጪ ለራሱ ማድረግ የማይችለውን አቅም ሳይኖረው ቀለብ እንድሰጥ ልገደድ አይገባም፡፡ ቀለብ ሲወሰን የቀለብ ሰጪውን የገንዘብ አቅም እና የተቀባዩ ችግር ግምት ውስጥ ሊያስገባ ይገባል፡፡ የአሁን ተጠሪ በየወሩ ከ10,000 ብር በላይ እያገኘ፣ ኮንዶሚኒየም ቤቱ የማይከራይ ሲሆን፣ እኔ በልብስ ቤት ተቀጥሬ በወር ከማገኘው 1000 ብር የማይበልጥ ገቢ 4000 ብር ቀለብ በወር እንድከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ የአሁን አመልካች ባቀረበችው አቤቱታ ከዚህ በፊት የልጅ ቀለብ እንድከፍል ሲወሰን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የኮንዶሚኒየም ቤት ለልጅ ቀለብ እንዲውል የተደረገ ሲሆን አሁን ግን ተከሳሽ የራሱ መተዳደሪያ ያለው እና ገቢ ያለው በመሆኑ ቀድሞ የምሰጠው የልጅ ቀለብ ሊቀነስልኝ ይገባል ስትል ጠይቃለች፡፡ ተከሳሽም የአሁን ተጠሪ አመልካች ተከሳሽ የሚያገኘው ገቢ ስትል ያቀረበችው አቤቱታ እጅግ የተጋነነ ነው፡፡ ይህን ያህል መጠን ገንዘብ አላገኝም፡፡ በመሆኑም አቤቱታዋ ውድቅ ይሁንልኝ በሚል መልስ ሰጥቷል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አከራክሮ በመ/ቁጥር 256800 ሚያዝያ 18 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ አመልካች የልጅ ቀለብ ይሻሻልልኝ ብላ ላቀረበችው አቤቱታ ተጠሪ ገቢው ጨምሯል በማለት ሲሆን ቀደም ብሎ የልጅ ቀለብ የተወሰነው የአመልካችን የገቢ ምንጭ በማየት እንጂ የተጠሪን ገቢ ሁኔታ በማጣራት አይደለም፡፡ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 203 የቀለብ መጠን በአንቀጽ 197 በተዘረዘሩት ምክንያቶች ሊሻሻል እንደሚችል ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት የቤት ኪራይ ሊቀንስም ሊጨምርም ስለሚችል የኑሮ ውድነትና ተያያዥ ጉዳዮች የቀለብ መጠን ለማሻሻል በቂ ምክንያት በመሆኑ አመልካች የልጅ ቀለብ ተሻሽሎ ብር 4000 ከሚያዝያ ወር 2013 ዓ/ም ጀምሮ ልትሰጥ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ ከሳሽ የአሁን አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬት አቅርባ አከራክሮ በመ/ቁጥር 275237 ጥር 5 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ቀደም ብሎ ቀለብ የተወሰነው የኮንዶሚኒየም ቤት ኪራይ ገቢን በተመለከተ ነው፡፡ አመልካች ኮንዶሚኒየም ቤቱ የግሏ መሆኑ ሲወሰንልኝ ተከራይ አስወጥቼ እየኖርኩበት ነው ብላለች፡፡ ቀደም ብሎ ቀለብ እንዲትሰጥ የተወሰነው የቀለብ ሰጪውን አቅምና ተቀባዩን ችግር በማየት ሲሆን የተከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ገቢ ማግኘት ልጁን ተጨማሪ ተጠቃሚ የሚያደርገው እንጂ የልጁን ቀለብ የሚያሳንስበት ሊሆን አይገባም፡፡ በመሆኑም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ ጸንቷል ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርቧል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የቀለብ ይሻሻልልኝ ጥያቄዋ ተቀባይነት ያጣው የሰበር አመልካች ያላት የተረጋገጠ ገቢ ከግንዛቤ ውስጥ ገብቶ መሆን አለመሆኑ ከፌደራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 203 እና 197 ድንጋጌዎች አኳያ ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ መጋቢት 6 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም መጋቢት 27 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታዋን በማጠናከር ተከራክራለች፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ባቀረበችው አቤቱታ ከዚህ በፊት የልጅ ቀለብ እንድከፍል ሲወሰን የኮንዶሚኒየም ቤት ገቢ ለልጅ ቀለብ እንዲውል ተደርጎ ሲሆን አሁን ግን ተከሳሽ የራሱ መተዳደሪያ ያለው በመሆኑ ቀድሞ የምሰጠው የልጅ ቀለብ ይቀነስልኝ ስትል የጠየቀች ሲሆን የስር ፍ/ቤቶችም የአሁን አመልካች ቀድሞ የኮንዶሚኒየም ቤት የጋራ በነበረ ጊዜ ኪራዩ ለልጁ ማሳደጊያ እንዲውል የተወሰነ መሆኑንና የአሁን ተጠሪ ገቢ ማግኘት ልጁን ተጠቃሚ የሚያደርግ እንጂ የአሁን አመልካች ቀድሞ የሚትሰጠወን ቀለብ የሚያስቀንስ በቂ ምክንያት አይደለም ሲሉ በወር 4000 ብር ቀለብ እንዲትሰጥ ወስነዋል፡፡ የአሁን አመልካች ቀድሞ ስትሰጥ የነበረው ቀለብ የጋራ ቤት ኮንዶሚኒየም ተከራይቶ ከሚገኘው ገብ መሆኑ አላከራከረም፡፡ ይህ ኮንዶሚኒየም ቤት አሁን የግሏ ንብረት ሆኖ የተወሰነ መሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ የአሁን አመልካች ቀለብ እንዲቀንስላት አንደ ምክንያት ያቀረበችው ኮንዶሚኒየም ቤት፣ ቀድሞ የጋራ ንብረት ሆኖ አመልካች ስትከፍል የነበረው ቀለብ አሁን የግሏ ንብረት ሆኖ ገቢዋ ጨምሯል የሚባል እንጂ ቀንሷል ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ የፌደራል የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አወጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 197 በዚህ ህግ አንቀጽ 198 ድንጋጌዎች መሰረት ቀለብ የመስጠት ግዴታ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ያለበት ሰው እንደ ባለጉዳዩቹ ሁኔታና እንደ አካባቢው ልማድ የሚስማማው በመከተል ለቀለብ ተቀባዩ ምግብ፣ መኖሪያ፣ ልብስ፣ ጤናውን የሚጠብቅበት እና እንደሁኔታው ለትምህርት አስፈላጊ የሆነውን ነገር መስጠት ያለበት መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ቀለብ ሲወሰን የቀለብ ሰጪውን የገንዘብ አቅም እና የተቀባዩን ችግር ግምት ውስጥ መግባቱ ተገቢ ነው፡፡ የቀለብ ሰጪ የገንዘብ አቅም ጠንካራ ከሆነ በዚያው መጠን የቀለብ ተቀባዩ ችግር ታይቶ ቀለብ የሚወሰን ይሆናል፡፡ የአሁን አመልካች የገንዘብ አቅሚ ባልቀነሰበት ቀድሞ ስትሰጥ የነበረውን ቀለብ ይቀነስልኝ አቤቱታ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የአሁን ተጠሪ የሚያገኘው ገቢ ቀለብ ተቀባዩ ልጃቸው እንደመሆኑ እና በአሁን ተጠሪ እንክብካቤ እያደገ እንደመሆኑ የቀለብ ተቀባዩን ችግር ለማቀላል የተሻለ ከሚሆን በቀር ለአሁን አመልካች ቀድሞ ስትሰጥ የነበረውን ቀለብ ለመቀነስ በቂ ምክንያት አይሆንም፡፡ በዚሁ መሰረት ተገንዝበው የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## ውሳኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 275237 ጥር 5 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 256800 ሚያዝያ 18 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
3. የካቲት 10 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመ/ቁጥር 256800 ላይ የተሰጠው የአፈጻጸም እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
4. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም